# የኅዳር ወር መዝሙራት

## እግዝእትየ

እግዝእትየ ውስተ ምድረ ነኪር ትሄልዊ
ገሊላ እትዊ /4 / ሀገረኪ ገሊላ እትዊ

ትርጉም፤ *በባዕድ ሀገር ያለሽ እመቤቴ ሆይ*
*ወደ ሀገርሽ ገሊላ ግቢ፤*

# ሥላሴን አመስግኑ

ሥላሴን አመስግኑ (2X)
የምድር ፍጥረታት ዘምሩ እልል በሉ } አዝማች...

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ
ምስጋና ይድረሰው ከምንም በፊት
ዓለማትን ሁሉ ለፈጠረ ጌታ
ምስጋና ይገባል ከጠዋት እሰከ ማታ

አዝማች...

ኪሩቤል ሱራፌል የሚያመሰግኑህ
መላእክት በሰማይ የሚዘምሩልህ
እኛም የአዳም ልጆች እንዘምራለን
በሰማይ በምድር እንጠራሃለን

አዝማች...

ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ
ሥላሴም አምባዬ ክብሬም ናቸውና
ሁሌ ይመሩኛል በሕይወት ጎዳና

አዝማች...

ብራብ በሥላሴ እጠግባለሁኝ
ብጠማም በአምላኬ እረካለሁኝ
ሥላሴም አምባዬ ክብሬም ናቸውና
ሁሌ ይመሩኛል በሕይወት ጎዳና

አዝማች...

# እመኑ በእርሱ

እመኑ በእርሱ ድንቅ ያደርጋል ጌታ
በረድ አዝንቦ ጠላት እየመታ
ውቅያኖስ ጥልቁን ፈጥኖ እያተነነ
ነገር ለወጠ ሁሉ በእርሱ ሆነ
} አዝማች...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመኑ በእርሱ) | ተራራው ነደደ | (እመኑ በእርሱ) | ሸለቆው ታወከ |
| «« | ዝግባው ተሰባብሮ | «« | አለቱ ደቀቀ |
| «« | የአሕዛብ ጣዖታት | «« | በፊቱ ረገፉ |
| «« | በስሙ የታመኑ | «« | ወጀቡን ቀዘፉ |

አዝማች...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመኑ በእርሱ) | የማይነጋ ሌሊት | (እመኑ በእርሱ) | የማያልፍ ቀን የለም |
| «« | ሁሉ ይቻለዋል | «« | ጌታ መድኃኔዓለም |
| «« | ፍቅር ነው ዘለዓለም | «« | ደግ አባት ለልጁ |
| «« | ሁሌም ተዘርግታ | «« | ትኖራለች እጁ |

አዝማች...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመኑ በእርሱ) | ሞገድ የማይሰብረው | (እመኑ በእርሱ) | ፅኑ መርከብ አለን |
| «« | አንፈራም አንሠጋም | «« | ከእርሱ ጋር እያለን |
| «« | ጠላት ተሸንፏል | «« | ሠይጣን አፍሯል ዛሬ |
| «« | ወህኒው ይነዋወጥ | «« | በታላቅ ዝማሬ |

አዝማች...

| | | | |
|---|---|---|---|
| (እመኑ በእርሱ) | ባዶ ነው አይሠራም | (እመኑ በእርሱ) | የጠላት ፉከራ |
| «« | የማይተወን ጌታ | «« | አለ ከእኛ ጋራ |
| «« | እጅግ አትረፍርፎ | «« | ፀጋን ከአበዛልን |
| «« | በሞት ጀርባ ቆመን | «« | ገና እንዘምራለን |

አዝማች...

# ከዳዊት ዘር

ከዳዊት ዘር የተገኘች
በቤተ መቅደስ ያደገች
በድንግልና የወለደች
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም አማላጅ ነች } አዝማች…

እሳተ ነበልባል የሆነውን ጌታ
የዓለሙን መድኅን ያንን ኃያል ጌታ
የወለደችልን ቅድስተ ቅዱሳን
ዛሬ እናመስግናት ድንግል ማርያምን

አዝማች…

ታላቅ ግርማ ያለው ጌታችን ኢየሱስ
ከአንቺ በመወለድ ዓለምን ለማደስ
ከዙፋኑ ወርዶ የዓለም ቤዛ ሊሆን
በአንቺ ላይ አደረ የዓለሙ ብርሃን

አዝማች…

ድንግል ሆይ መጥተናል ልንማጸንሽ
እንድታማልጅን ከኃያሉ ልጅሽ
ፀሎት አድርጊልን ማርያም እናታችን
ፍቅርን እንዲሰጠን ቅዱስ አባታችን

አዝማች…

# በልዎ ለእግዚአብሔር

<u>በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ</u> (2X)
<u>እግዚአብሔርን በሉት ስራህ ግሩም ድንቅ ነው</u> (2X) } **አዝማች...**

ሰማያትን በስንዝር የምትለካቸው (ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው)
ቀላያትን በእፍኝህ የምትሰፍራቸው ««
ቃልን ብቻ ልከህ የምታሰማምር ««
በድንቅ አሰራረህ ግሩም ነህ እግዚአብሔር ««

**አዝማች...**

ለእኔ የዋልክልኝ መቼ የሚረሳ ነው (ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው)
ከሰው መቆጠሬ ጌታዬ በአንተ ነው ««
በላዬ ዘርግተህ የክብርን ደመና ««
ቅጥሩን አዘለልከኝ ድጋፍ ሆንከኝና ««

**አዝማች...**

እሰግድልሃለሁ ፊትህ ተንበርክኬ (ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው)
ውለታህ ማርኮኛል እግዚአብሔር አምላኬ ««
ከአንተ ጋራ ሆኜ ምን ይጎልብኛል ««
በምኅረትህ ጎብኘኝ ጸጋህ ይበቃኛል ««

**አዝማች...**

ስለኃጢአቴ ብዛት ሊወግሩኝ ሲነሱ (ሥራህ ግሩም ድንቅ ነው)
ከፊቱ አቁመውኝ ሲከሱኝ በብዙ ««
ጥፋቴን አይሻም እርሱ መቼ ፈረደ ««
ውለታው ግሩም ነው ሊምረኝ ወደደ ««

**አዝማች...**

# ከደመናት በላይ

ከደመናት በላይ የሚመላለሰው
የእሳት ማዕበል በፊቱ የሚፈሰው
ሃገሩ ወዴት ነው ስሙስ ማን ይባላል
ወደር የሌለው ነው ማን ይመስለዋል

አዝማች…

ስሙስ እግዚአብሔር ነው ጌታ ጸባዖት
የሚታዘዙለት ኃይላት ሥልጣናት
አሮን መልከ ጸዴቅ ጴጥሮስ ካህናቱ
የሚያከብሩት ንጉሥ ግሩም ለፍጥረቱ

አዝማች…

እንደ ፏፏቴ ነው የድምፁ ሞገድ
ከአፉ ሠይፍ ይወጣል እሳት የሚነድ
በሰማይ ደመና የሚረማመድ
በትንሽ ትልቁ ልብ የሚወደድ

አዝማች…

ከፍ ባለው ዙፋን በሰማይ ተቀምጦ
ፍጥረቱን ይገዛል በእፍኙ ጨብጦ
የምድር ነገሥታት ዘውዳችሁን አንሱ
ለቅድስት ሥላሴ እጅ እንድትነሱ

አዝማች…

ከጥልቁ ነው ሲሉት ይኖራል በላይ
በምድር ነው ሲሉት አለ በሰማይ
ወሰን የሌለው ነው ለሃገር ግዛቱ
ሲመሰገን ያድራል በክብረ መንግሥቱ

አዝማች…

# አንተኑ ሚካኤል

**አንተኑ ሚካኤል / 2□/**
*መና /2/ ያወርድክ*
**ዘአውረድከ መና /2/ ሚካኤል /2/ ዘአውረድከ መና/2/**

# የማትቀየር አንተ ብቻ

ያለ አንተ ለእኔ ማን ሊሆነኝ
ጌታ ሆይ ፍቅርህ ልቤን ነካኝ
ሕግህ ነበረ የአፌ መፍቻ
የማትቀየር አንተ ብቻ (2X) } **አዝማች...**

አስተምርበት በመርከቤ
ቃልህን ብቻ ያጥምድ ልቤ
ቀኑ ቢከፋም ወደ ማታ
ዓሣው ታዘዘ ለአንተ ጌታ

**አዝማች...**

ውዴ ልበልህ ሸልማቴ
ቤቴም የአንተ ነው ሰውነቴ
ደለደልክልኝ ያንን ጋራ
እንዳልሞት አርገኝ እንዳልፈራ

**አዝማች...**

ፀፀተኝ ዛሬ ያኛው ወራት
አንተን ሳላውቅህ የኖርኩበት
ፍቅር ነህ ለካ ማር ወለላ
ምን ሕይወት አለ ከአንተ ሌላ

**አዝማች...**

ቀሳፊያችንን ቀስፈኸዋል
ያን የጭንቁን ቀን አልፈነዋል
ነገም የአንተ ነው አዲሱ ቀን
እንዘምራለን ስትናፍቀን

**አዝማች...**

# እግዚአብሔር መልካም ነው

እግዚአብሔር መልካም ነው
በመከራ ቀን መሸሸጊያ ነው } **አዝማች...**

ከገነት ሲሰደድ አዳም አባታችን
ሞት ነግሦብን ሳለ በኛ በሁላችን
ቃል እንደገባለት ተወልዶ ሊያድነው
በመከራው ጊዜ መሸሸጊያ ሆነው (2X)

**አዝማች...**

አብርሃም ከካራን ከእናት ከአባቱ ቤት
ከነዓን ሲገባ ሲሰደድ በእምነት
ከተሰጠው ተስፋ አንዳች ሳይጎድልበት
እንደምድር አሸዋ ዘሩን አበዛለት (2X)

**አዝማች...**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቀን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

**አዝማች...**

በኃዘን በችግር በመከራ ጊዜ
ጭንቀን የሚያርቅ ነው የነፍሴን ትካዜ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
እግዚአብሔር መልካም ነው ኃዘኔን አስረሳኝ
የቀደመው እባብ ሰላሜን ሲነሳኝ
ክርስቶስ ኢየሱስ ኃዘኔን አስረሳኝ (2X)

አዝማች...

# ገብርኤል ኃያል

ገብርኤል ኃያል መልአከ ሰላም መልአከ ብሥራት
የምታወጣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሚነድ እሳት
ፍቅርህ ተስሏል በልባችን
ፊትህ ቆመናል ባርከን ብለን } አዝማች...

የጽናታቸው ዝናው ሲሰማ
ከዚያች ባቢሎን ከሞት ከተማ
ሕፃናት ሳሉ በራ እምነታቸው
ቆመህ ተገኘህ መሐከላቸው

አዝማች...

ውሃው ሲዘልል ቢያስደነግጥም
በጋኖችም ውስጥ ቢነዋወጥም
ጸንተው ዘመሩ ልጅና እናቱ
አንተ ስትደርስ ከዛ ከእሳቱ

አዝማች...

ቂርቆስም ጸና ሞትን ሳይፈራ
አንተ ስላለህ ከነሱ ጋራ
አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ
አምነው ድል ነሱ ያንን መከራ

አዝማች...

እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ
ቆመህ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ
ክፉውን ዘመን የማልፍበት
ጽናትን ስጠኝ ድል ልንሳበት

አዝማች...

# ለውዳሴሽ ልትጋ

ለውዳሴሽ ልትጋ ስምሽ ግርማ አለው (2X)
እመቤቴ (ኧኸ) እመቤቴ ስልሽ እውላለሁ } አዝማች

ከልቤ አቀርባለሁ ምስጋና ለስምሽ
መማጸኛዬ ነው ጽኑ ቃል ኪዳንሽ
በሰላምታ ድምፅሽ ያልጸና ማን አለ
ፅንሱ በማኅፀን በደስታ ዘለለ

አዝማች…

ማርና ወተት ነው የስምሽ ስያሜ
እመቤቴ ስልሽ ይቀላል ሸክሜ
ቅኔ ማህሌቱ ሰዓታት መዝሙሩ
ያመሰግኑሻል ምድርና ጠፈሩ

አዝማች…

እናቱ ነሽና አንቺ ለአዶናይ
ማለድኩኝ ከፊትሽ ይቅርታውን እንዳይ
ሰኣሊ ለነ ብዬ ይኸው ተርፌአለሁ
ስምሽን ጠርቼ ነገም እኖራለሁ

አዝማች…

ነይ ነይ እልሻለሁ እንደ ካህናቱ
በሰዓታት ጸሎት ቆሜ በሌሊቱ
ዝም አልልም እኔ አወድስሻለሁ
የዓለምን መከራ እረሳብሻለሁ

አዝማች…

# ምስጉን ነው የተመሰገነ

ምስጉን ነው የተመሰገነ
ባሪያውን እኔን ይቅር ያለ
ይመስገን ይመስገንልኝ
ጎጆዬን አምላክ ሞላልኝ } **አዝማች…**

እጅህ ሰፊ እንደሆነ አውቃለሁ ጌታዬ
የጎደለው ሞልቷል ይድረስ ምስጋናዬ
ያጣሁትን ከአንተ አግኝቻለሁ
ሁሉም ነገር ለበጎ ብያለሁ (2X)

**አዝማች…**

ማቄን የቀደደው ደስታ አስታጠቀኝ
ባዶ የነበርኩት ሁሉም ተሰጠኝ
ሰጭም ነሽም እግዚአብሔር ብቻ ነው
የሰው ድርሻው በር ማንኳኳት ነው (2X)

**አዝማች…**

እገፋለሁ እንጂ እኔ አልጨነቅም
መሠረቴ አንተ ነህ ከቶ አልናወጥም
ስትሰጠኝ የሚታየውን
እንዳትነሳኝ የዘለዓለሙን (2X)

**አዝማች…**

ቢሰጥ አያልቅበት ለጋስ ክቡር ጌታ
ሁሉን ከወነልኝ በልዩ ችሮታ
ድሆች ስንሆን ሁሉም አለንና
ለአምላካችን ይድረሰው ምስጋና (2X)

**አዝማች…**

# እፁብ ድንቅ ነው ውለታው

እፁብ ድንቅ ነው ውለታው
እግዚአብሔር ለእኛ ያረገው
ከቶ አይጥለንም ለዘለዓለም
እንደ አምላካችን ማንም የለም } አዝማች…

ወድቀን ነበረ ተነስተናል
ባሕር አቁሞ አሻግሮናል
ድንቅ አደረገ ተዓምር ሠራ
እያንሳፈፈ ያን ተራራ

አዝማች…

የጠፋውን በግ እየፈለገ
ራሱን ባዶ አደረገ
መስቀል ታቅፎ ክንዱ ዛለ
ምን ያልሆነልን ነገር አለ

አዝማች…

ከአባትም በላይ አባት ነው
የልጆቹ እንባ የሚገደው
የጭንቀታችን ተካፋይ
አዛኝ ጌታ ነው ሁሉን ቻይ

አዝማች…

ዳግም እንድንቆም በሕይወት
ጨክኖ ወደደን እስከ ሞት
ከእንግዲህ አንፈራም እንጸናለን
ለክፉ የማይሰጥ አባት አለን

አዝማች…

# ሥጋዋን አንፅቶ

ሥጋዋን አንፅቶ በማርያም የአደረ
ቃሉን በነቢያት ቀድሞ ያናገረ (2X)
ቀድሞ ያናገረ

ቃል በቃሉ ተናገራት (2X)
ማርያምን አከበራት እግዚአብሔር መረጣት } አዝማች…
ቃል ተናገራት

ፍጥረታት በሙሉ ይመሰግኑሻል
የሕይወታችን በር ድንግል ናት ይሉሻል (2X)
ድንግል ናት ይሉሻል

አዝማች…

እግዚአብሔር አብ ላከ አንድያ ልጁን
ያንቺን ሥጋ ለብሶ እኛን እንዲያድን (2X)
እኛን እንዲያድን

አዝማች…

ድንግል ሰገዱልሽ መላእክት በራማ
በአንቺ ላይ ስለ አለ የመላእከት ግርማ (2X)
የመላእከት ግርማ

አዝማች…

ዓለምን የአዳነ የአንቺን ሥጋ ለብሶ
ዘለዓለም ኗሪ ነው በሰማያት ነግሦ (2X)
በሰማያት ነግሦ

አዝማች…

# የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው

የጠሩሽ አንቺን ተማጽነው የዳኑብሽ
የበላየሰብዕ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት } አዝማች...

በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ፅድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል (2X)

አዝማች...

እኔም በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አትርሽኝ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ (2X)

አዝማች...

እኛም በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢን እንላለን
በአማላጅነትሽ እንድናለን (2X)

አዝማች...

ምዕመናንም በአንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢን ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናሉ (2X)

አዝማች...

# አሜን እግዚአብሔር ከብሯልና

አሜን እግዚአብሔር ከብሯልና
ምድርን ሸፈናት በምስጋና
አሜን እግዚአብሔር ከብሯልና
ምድርን ከደናት በምስጋና

ማሰማሪያዎቹ መንጎቹን ለበሱ
በክብር ተሞልቷል ገናናው መቅደሱ
እልል እልል በሉ ድምጻችሁ ይሰማ
በእልልታ ወረስናት ኢያሪኮንማ

**አዝማች...**

አባናና ፋርፋ የሶርያ ወንዞች
አልቻሉም በጭራሽ ማዳን ሕመምተኞች
የእግዚአብሔር ሰው ኤልሳዕ ቃል ብቻ ተናገር
ንዕማን እንዲመሰጥ በአምላካችን ፍቅር

**አዝማች...**

ዘመን አያስረጇት ዓመታት ወራት
ዛሬም በሰማይ ነው በአሸናፊነት
የነገድ አለቆች ያመሰግኑታል
የወርቁም መሰዊያ በእጣን ተሞልቷል

**አዝማች...**

ሜዳና ተራራው በወንጌል ታረሰ
ዳጎን ተሰባብሮ እግዚአብሔር ነገሰ
ይሰበካል ገና የመንግሥቱ ዜና
የአምላካችን መምጫው ጊዜው ቀርቧልና

**አዝማች...**